# *በቤት ልማት ፕሮግራም መሳተፍ ለሚፈልጉ*

# *ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ መረጃ*

ግንቦት 2007

የኢፌዴሪ ኤምባሲ

በርሊን

1- መግቢያ ገፅ 2

2- ትርጓሜ ገፅ 2

3- ስለ ምዝገባ መስፈርት ገፅ 3

4- የምዝገባ ቦታ ገፅ 4

5- በግል በማሕበር በመደራጀት ማመልከት ስለሚቻልበት አግባብ ገፅ 5

6- የባንክ ሂሳብ አከፋፈት ገፅ 8

7- ገንዘብ ከግል የዲያስፖራ የውጭ ምንዛሪ ወደ ማሕበሩ ዝግ አካውንት የሚገባበት ሁኔታ ገፅ 8

8- የስራ ፍሰት ገፅ 9

9- በማሕበራት ስም ለቤቶች ግንባታ በዝግ ሂሳብ የተቀመጠን ገንዘብ ስለማንቀሳቀስ ገፅ 10

10- የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ ገፅ 10

11- የቤቶች ግንባታ ቁጥጥርና ክትትል ገፅ 11

12- የመኖሪያ ቤቶች ርክክብ ገፅ 11

13- የመመዝገቢያ ቅፆች ገፅ 12

14- የመተዳደርያ ደንብ ይዘት ገፅ 13

15- የሚገነቡ የቤቶች ዓይነት፣ ስፋትና የቤቶች ዋጋ ገፅ 15

## 1-መግቢያ

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከትውልድ አገራቸው ለማስተሳሰር፣ በልማቱና በዲሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ ተጠቃሚና ተሳታፊ ለማድረግ በመንግስት በኩል ትኩረት ተሰጥቶ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ዲያስፖራውን ከሀገሩ ጋር በማስተሳሰር ተጠቃሚ እንዲሆንና በሀገሩ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ለማስቻል የዲያስፖራ ፖሊሲ በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግ የተጀመረ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ የቤት ልማት ፕሮግራም አንደኛውና ዋነኛው ነው፡፡

ክልሎችና የአስተዳደር ከተሞች የቤት ልማት ፕሮግራሙን ለማስፈፀም መመሪያ፣ የማሕበራት መተዳደሪያ ደንብና ልዩ ልዩ ቅፆች በማዘጋጀት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን ያሳወቁ ሲሆን የአዲስ አበባ መስተዳድር ዝግጅት ሲጠናቀቅ በተመሳሳይ ለተጠቃሚዎች የሚገለፅ ይሆናል፡፡

የበርሊን ሚስዮን በሚከታተላቸው የጀርመን ክልሎችና በተወከለባቸው ሀገሮች (ፖላንድ፣ ቼክና ስሎቫክ) የምትገኙ የዲያስፖራ አባላት ሁሉ ከሰኔ 1/2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚቀጥሉት ስድስት ወራት ድረስ በቤት ልማት ፕሮግራሙ ላይ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪውን እያስተላለፈ በዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን የምትፈልጉ በበርሊን ሚስዮን ዘወትር ሮብና ሓሙስ ከ13፡30 ጀምሮ እስከ 16፡00 ሰዓት ድረስ በሌሎች የምዝገባ ጣቢያዎች ደግሞ የምዝገባ አስተባባሪዎች በሚገልፁት ጊዜ እየተገኛችሁ እንድትመዘገቡ እያሳሰብን ለምዝገባው ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች፣ የመመዝገቢያ ቅፆችና የቤት ሕብረት ስራ ማሕበራት መተዳደሪያ ሞዴል ደምብ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 2-ትርጓሜ

- ***ዲያስፖራ*** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነው፣
- ***ሃዋላ*** ማለት በውጭም ሆነ በሃገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ወይም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካኝነት ገንዘብ የመዘዋወሪያ ዘዴ በኢትዮጵያ የባንክ አሰራር ዕውቅና የተሰጠው ነው፣
- ***ዲፕሎማቲክ ፓውች*** ማለት በቪየና ኮንቬንሽን መሰረት ለአንድ ሚስዮን ኦፊሴላዊ ስራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሰነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ነው፣
- ***ሚሰዮን*** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ ወይም ቀዋሚ መልእክተኛ ፅ/ቤት ወይም ቆንስላ ፅ/ቤት ነው፣

- ***ነባር የመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበር*** ማለት በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅቶ በዝግ ሂሳብ ገንዘብ ያስቀመጠ፣ በማህበራት ማደራጃ የምዝገባ ሰርተፊኬት ያለውና እስካሁን ድረስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ያልተረከበ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ነው፣

- ***አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር*** ማለት በማህበር በመደራጀት ታውን ሃውስ እና አፓርትመንት ቤቶችን ለመገንባት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለመመዝገብ የወጣው የምዝገባ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2006 ፀድቆ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ መልክ የሚቋቋም የቤት ስራ ማህበር ነው፣

- ***በግል ተመዝጋቢ*** ማለት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በታውን ሃውስ በተናጠል ተመዝግቦ በጋራ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ የሚሆንበት ስርዓት ነው፣

- ***የውክልና ማስረጃ*** ማለት በህግ የተደነገገ ስርዓት ተከትሎ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል/ውልና ማስረጃ እና ሚስዮን በአካል ቀርቦ የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሰነዶች ማረጋገጫ መስሪያ ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ነው፣

- ***ዲፕሎማት*** ማለት በኢፌደሪ ሚስዮኖች በውጭ ግንኙነት መስክ ተመድቦ የሚያገለግል ኢትዮጵያዊ የመንግስት ሰራተኛ ነው፣

- ***ሎካል ሰራተኛ*** ማለት በሃገር ቤት ተቀጥሮ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሚስዮን ተመድቦ እያገለገለ የሚገኝ ሰራተኛ (non-diplomatic staff) ነው፣

- ***ተመላሽ ዲያስፖራ*** ማለት ለተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ተመልሰው በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነው፣

- ***የማህበራት ማደራጃ*** ማለት በአስተዳደሩ/በክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የህብረት ስራ ማደራጃና ልማት አብይ የስራ ሂደት ነው፣

- ***ታውን ሃውስ*** ማለት ጂ1 ወይም ጂ2 ወለል ያለው ራሱን የቻለ መጠነኛ ግቢ እና መግቢያ ያለው የመኖሪያ ህንፃ ሲሆን ከአጎራባች መኖሪያ ቤቶች ጋር በግድግዳ የተያያዘ መኖሪያ ቤት ነው፡፡

## <u>3. ስለ ምዝገባ መስፈርት</u>

3.1 በግል ተመዝጋቢም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ተደራጅተው ቤት ለመገንባት ፍላጐት

ያላቸው በውጭ አገር የሚኖሩ **ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያውያን** የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፣

- ❖ የፀና የፓስፖርት ቅጅ፣
- ❖ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣ (ለትውልድ ኢትዮጵያውያን)
- ❖ የሚኖርበት አገር የመኖሪያ ፈቃዱ ወይም የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ አደረጃጀቶች ባሉባቸው አገሮች የኮሙኒቲ ማኅበር አባልነት መታወቂያ ካርዱ ወይም በሚሲዮኑ የሚሰጥ ማስረጃ፣
- ❖ ያገባ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጅውን፣
- ❖ ያላገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
- ❖ ሁለት የፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፣
- ❖ ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅፆችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
- ❖ ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተደደር ውስጥ የመኖሪያ ቤት ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- ❖ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ /ዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ/ የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃዱ ለመውሰዱ ዝግጁ የሚሆን፣
- ❖ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ፣

**3.2. በሚሲዮኑ ተመድበው የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች**

- ❖ የፀና የፓስፖርት ቅጅ፣
- ❖ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣
- ❖ የሚሲዮኑ ሠራተኛ ስለመሆኑ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከሚሲዮኑ የሚሰጥ ማረጋገጫ፣
- ❖ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በኢትዮጵያ ብር የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% በመክፈል ዝግጁ የሚሆን፣

- ❖ ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤት ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣

## 4. የምዝገባ ቦታ

- ❖ የበርሊን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮን በሚከታላቸው የጀርመን ክልሎችና በተወከለባቸው ሃገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የሚመዘገቡት ሚሲዮኑ ዘንድ በአካል በመገኘት ነው፡፡
- ❖ የበርሊን ሚሲዮን ከሚከታተላቸው የጀርመን ክልሎች ውስጥ ርቀት ባላቸው ከተሞች የሚገኙ የዲያስፖራ አባላት በየከተሞቹ ወደ ተደራጁ ማሕበራትና አስተባባሪዎች በአካል በመቅረብ ብቻ ይመዘገባሉ፡፡ ለምሳሌ በሃምቡርግና አካባቢዋ የሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት ሃምቡርግ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ መመዝገብ ይችላሉ፡፡ በሌሎች የጀርመን ከተሞች የሚገኙ ተመዝጋቢዎች ለወደፊት በሚገለፁ የምዝገባ አስተባባሪዎች በኩል ይመገባሉ፡፡
- ❖ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮን በተወከላበቸው አገሮች በፖላንድ፣ በቼክ ሪፐብሊክ እና በስሎቫክ የሚገኙ የዲያስፖራ አባላት በአካባቢው በተለያየ አገባብ በተደራጁ ማሕበራት በኩል ይመዘገባሉ፡፡
- ❖ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ በርሊን ሚሲዮን የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች ምዝገባውን በሚሲዮኑ በማድረግ መረጃውን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡

## 5-በግል ወይም በመኖሪያ ቤት ስራ ማሕበር በመደራጀት ማመልከት ስለሚቻልበት አግባብ

### 5.1 በግል አመልክተው በሚስዮኑ ወይም በውጭ ጉዳይ ሚር በኩል በማሕበር የሚደራጁ የመኖሪያ ቦታ ተመዝጋቢዎች

- ❖ በግል የሚመዘገቡ የዲያስፖራ አባላት የሚፈልጉትን ክልል/ከተማ አስተዳደር በመምረጥ የሚፈልጉትን የቤት ዓይነት ይመርጣሉ፣
- ❖ ቤቱን ለመገንባት ከሚያስፈልገው ወጪ የሚጠበቅባቸውን 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት ከሚኖሩበት ሀገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ በመክፈት ገንዘብ በውጭ

ምንዛሪ ወደ አገር ቤት በመላክ ወደ ተከፈተው አካውንት ያስተላለፉበትን ደረሰኝ ቅጂ ተሞልቶ ከተፈረመው የመመዝገቢያ ቅፅ ጋር በማያያዝ ለሚሲዮኑ ያቀርባሉ፣

- ❖ በግል የተመዘገቡት የዲያስፖራ አባላት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ዝቅተኛውን ቁጥር ሲያሟሉ ሚሲዮናችን በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ወደ ዋናው መ/ቤት የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይልካል፡፡
- ❖ የግል ተመዝጋቢዎች በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር በማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት በማህበር ዝቅተኛ ቁጥር የማይሞሉ ከሆነ ከሚሲዮናችን መረጃቸው በሸኚ ደብዳቤ ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡
- ❖ በግል የመጡ መረጃዎችን ወደ መረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር በዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡

## 5.2 በግል የመኖሪያ ቦታ ተመዝጋቢ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች

- ❖ በግል የሚመዘገቡት ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች የሚፈልጉትን ክልል/ከተማ አስተዳደር ለመምረጥ የሚፈልጉትን የቤት ዓይነት ይመርጣሉ፣
- ❖ ቤቱን ለመገንባት ከሚያስፈልገው ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል አካውንት በመክፈት በብር ያስቀመጡበትን ማስረጃ ተሞልቶ ከተፈረመው የምዝገባ ቅጽ ጋር ለሚሲዮናችን ያስረክባል፡፡ ሚሲዮናችን በመሸኛ ለሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡
- ❖ በግል የተመዘገቡት ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ይፈጸማሉ፡፡ ለማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ይላካል፡

## 5.3 በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው የሚመዘገቡ የዲያስፖራ አባላት፤

- ❖ በመጀመሪያ መደራጀት የሚፈልጉትን ክልል/ከተማ አስተዳደር ይመርጣሉ፣
- ❖ በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የአባላቱን ቁጥር ይወስናሉ፣
- ❖ የመስራችን ስብሰብ በመጥራት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማህበራቸውን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተው ያፀድቃሉ፣

- ❖ በምስረታ ስብሰባው የሥራ አመራር ም/ቤት፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የቴክኒክና የማህበራዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማሉ፡፡ የአመራር አባላትም ምርጫ ያደርጋሉ፡፡

- ❖ ሁሉም የማህበሩ አባላት የመስራች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመስራች አባላት ዝርዝር ቅጽ ላይ ፊርማቸውን ያኖራሉ፡፡

- ❖ ማህበሩ በህጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር መመዝገብ የሚችለው የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ /ዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ/ በምዝገባ ወቅት መክፈል ሲችሉ እና መሬት ተዘጋጅቶ ማህበሩ ሲረከብ የቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ የሚከፍል፤

- ❖ ማህበሩ የእያንዳንዱ አባል የተሟላ ሰነዱና ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንኩ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ በማያያዝ በሚሲዮኑ የሚመዘገብያ ቦታ ወይም በተደራጁ የዲያስፖራው ማሕበራት ዘንድ በአካል ተገኝተው ምዝገባ ያካሂዳሉ፡፡

- ❖ የዲያስፖራው ማሕበራት መስፈርቱን አሟልተው የተደራጁ ማህበራትን ሰነድ ከተቻለ በአካል ካልሆነም በተመዘገበ ፖስታ ለሚሲዮናችን በአድራሻ ይልካሉ፡፡ ስለመድረሱ መተማመኛ ከሚሲዮኑ ይረከባሉ፡፡ ለማህበሩ የመተማመኛውን ኮፒ ይሰጣሉ፡፡

- ❖ ሚሲዮናችን የተደራጁ ማህበራትን ሙሉ መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በፖውች ይልካል፡፡ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉም የማህበራቱን ሰነዱ ስለመድረሱ ለሚሲዮኑ ያሳውቃል፡፡

- ❖ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበሩ እውቅና ማግኘቱን ለማህበሩ መሬት የግንባታ ፈቃዱ መዘጋጀቱን ለሚሲዮናችን ይገልጻል፡፡ ሚሲዮናችንም ይህንኑ ለማህበራቱ ያሳውቃል፡፡

- ❖ ማህበሩም ሁሉም አባላት ቀሪውን 50% ወደ ማህበሩ ዝግ አካውንት ማስተላለፋቸውን በማረጋገጥ መረጃውን ለሚሲዮናችን ያሳውቃሉ፡፡

- ❖ ሚሲዮናችን ቀሪውን 50% ክፍያውን ፈጽመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያስተላልፋል፡፡

## 6. የባንክ ሂሣብ አከፋፈት

- በቤት ልማት ፕሮግራሙ ለመሳተፍ የሚፈልጉ የዳያስፖራ አባላት በግላቸው በአገር ቤት በንግድ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አካውንት እንዲከፈትላቸው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለሚሲዮናችን ወይም ለተደራጀ የዲያስፖራ ማሕበር ቤት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

- ሚሲዮናችን በቀጥታ ከዲስፖራ ማሕበራት የደረሱትን የዳያስፖራ አባላት የውጭ ምንዛሬ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስተላልፋል፡፡

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደረሰው መረጃ መሠረት ለዳያስፖራ አባላቱ የግል የባንክ ሂሳብ መከፈቱን ለሚሲዮናችን ያሳውቃል፡፡

- ሚሲዮናችን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደረሰውን የአካውንት መረጃ በሚሲዮናችን የተመዘገቡ የዳያስፖራ አባላትንና ለዲስፖራ ማሕበራት ያሳውቃል፡፡

- የዳያስፖራ አባላቱ በሚሲዮናችን በኩል የደረሳቸውን የግል የባንክ አካውንት በመጠቀም ለመረጡት የመኖሪያ ቤቶች የግንባታ ወጪ የቅድሚያውን 50% በውጭ ምንዛሪ ያስተላልፋሉ፡፡

## 7. ገንዘብ ከግል የዳያስፖራ የውጭ ምንዛሪ ወደ ማህበሩ ዝግ የብር አካውንት የሚገባበት ሁኔታ

- ሚሲዮናችን በተሰጠው ውክልና መሠረት ለማህበራቱ ዝግ የብር የማህበር አካውንት እንዲከፈት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማህበራቱን መረጃ በማያያዝ ይጠይቃል፡፡

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚሲዮናችን በቀረበው ጥያቄ መሠረት ለማህበራቱ ዝግ የብር ሂሳብ በመከፈት ለሚሲዮናችን ያሳውቃል፡፡

- ሚሲዮናችን  ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደረሰው መረጃ መሠረት ለማህበራት የተከፈተ የአካውንቶች ቁጥሮች ለማህበራቱ አመራሮች ወይም  ለሕዳሴ ምክር ቤቶች በመግለጽ ሁሉም የማህበሩ አባላት የቤቱን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ እንዲያስገቡ  ያሳውቃል፡፡

- የማህበሩ አመራር አባላት ከዚህ በፊት በግላቸው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከከፈቱት የውጭ ምንዛሪ አካውንት ወደ ተደራጁበት ማህበር ዝግ የብር አካውንት እንዲያስገቡ ያሳውቃሉ፣

- የዳያስፖራ አባላቱም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከከፈቱት የግል የውጭ ምንዛሪ አካውንት ወደ ተከፈተው የማህበራቸው ዝግ የብር አካውንት የግንባታ ወጪ 50% ገንዘብ እንዲገባ ያዛሉ፣

- ❖ የማህበራቱ አመራር አባላት ወይም የዲያስፖራ ማሕበር አመራሮች ሁሉም የማህበሩ አባላት የቤቱ ግንባታ ወጪ 50% ወደ ማህበሩ አካውንት አስገብተው ሲያጠናቅቁ ማጠናቀቃቸውን ለሚሲዮናችን ያሳውቃሉ፣

- ❖ ሚሲዮናችን የቤቱ የግንባታ ወጪ 50% ከግል አካውንታቸው ወደ ማህበራቱ አካውንት አዛውረው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ማህበራቱ የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ይልካል፣

- ❖ የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን ለሚሲዮናችን ይልካል፣

- ❖ ሚሲዮኑ የደረሰው የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማህበራቱ አመራር አባላትና ለዲያስፖራው ማሕበራት አመራር ያሳውቃል፣

- ❖ የማህበራቱ አመራር አባላት ወይም የዲያስፖራው አመራር አባላት ሁሉም የማህበሩ አባላት የቤቱ ቀሪውን 50% ወደ ማህበሩ አካውንት አስገብተው እንዲያጠናቅቁ ያደርጋሉ፡፡ ሁሉም አባላት ክፍያውን ሲያጠናቅቁ ማጠናቀቃቸውን ለሚሲዮናችን ያሳውቃሉ፣

## 8. የሥራ ፍሰት (Work Flow)

በአጠቃላይ በሚሲዮናችን የዲያስፖራ መኖሪያ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲገባ የሚኖረን የሥራ ፍሰት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- ❖ ስለ መኖሪያ ቤቶች ልማት ፕሮግራም የሚመለከቱ መረጃዎች፣ ቅጾች፣ የመዘገቡበት ጊዜ ወዘተ ለዲያስፖራ ማድረስ፣

- ❖ በዲያስፖራ ቤቶች ልማት ፕሮግራም የሚፈልጉ አስፈላጊውን ቅጾች በመሙላት ለመመዝገብ ወደ ተመረጡ ከተሞች ወይም ወደ ሚሲዮናችን በአካል በመቅረብ ያመለክታሉ፣

- ❖ ሚሲዮናችን በመመሪያው መሠረት ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው የቀረቡ የዲያስፖራ አባላትን መረጃ አረጋግጦ በማህበሩ ስም ይቀበላል፣

- ❖ የማህበሩ መረጃዎች በሶስት ቅጂ /ለማህበሩ ተወካዮች የሚሰጥ፣ ለማህበራት አደራጅ አካል/ የሚተላለፍና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፋይል የሚደረግ/ ተረክቦ ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይልካል፣

- ❖ የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ክልል/ከተማ አስተዳደር የደረሰውን መረጃ የእውቅና ሰርተፊኬት ለሚሲዮናችን ይልካል፣

- ሚሲዮናችን መረጃውን ለተመዝጋቢ የዲያስፖራ አባላት ይልካል፣
- እውቅና የተሰጣቸው ማህበራት እያንዳንዱ አባላት በሚሲዮኑ በሚገለፀው መሠረት የሚጠበቅባቸውን ቀሪ 50% በማህበሩ አካውንት ያስገባሉ፣
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀረውን 50% በአጠቃላይ 100% በማህበራቸው ያስገቡ የዲያስፖራ አባላት ለክልል/ከተማ አስተዳደር ማህበራት አደራጅ አካል እና ለሚሲዮናችን ያሳውቃል፣

## 9. በማህበራት ስም ለቤቶች ግንባታ በዝግ ሂሳብ የተቀመጠን ገንዘብ ስለማንቀሳቀስ፣

የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የባንክ ሂሳብ በመተዳደሪያ ደንብና በክልል / አስተዳደር ማህበራት እንዲያደራጁ ስልጣን የተሰጠው አካል፣ በማህበሩ አመራር አካላት ወይም በተወካዮች አማካኝነት እንዲንቀሳቀስ ሲፈቅድና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደብዳቤ ሲጻፍ ብቻ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

## 10-የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ

### 10.1 የቤቶች ዲዛይን

ሁሉም ክልሎችና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የዳያስፖራ መኖሪያ ቦታ ዲዛይን በማዘጋጀት ለማህበራት ያቀርባሉ፡፤

የምዝገባ ሂደቱን አጠናቀው መሬት እና የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው ማህበራት ዲዛይንና ግንባታ በተመለከተ ሁለት አማራጮች ይኖራቸዋል፡፡ እነርሱም-

♦ክልሉ/ከተማ አስተዳሩ ባዘጋጀው ዲዛይን መሰረት ዲዛይኑን መቀበላቸውን በማረጋገጥ ወደ ተግባር መግባት፣

♦የተደራጁት የዲያስፖራ ማህበራት የክልሉ/የከተማ አስተዳደሩ ባለው የአካባቢ ፕላን መሰረት የራሳቸውን ዲዛይን አዘጋጅተው ማቅረብ ይችላሉ፡፡ የማህበራቱ አባላት ያቀረቡት የዲዛይን ማሻሻያ በክልሉ/በከተማ አስተዳደሩ አግባብነት ባለው አካል ሲፀድቅ ወደ ተግባር መግባት ይችላሉ፡፡ በዲዛይን ለውጥ የሚፈጠር የዋጋ ልዩነት ካ የየማሕበራቱ አባላት ከግንባታ በፊት በማሕበራቱ ዝግ አካውንት ያስገባሉ፡፡

### 10.2 የቤቶች ግንባታ

የዲዛይን ሂደቱን ያጠናቀቁ ማህበራት ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን ወይም ራሳቸው አዘጋጅተው ባስፀደቁት ዲዛይን መሰረት ወደ ግንባታ ለመግባት ሁለት አማራጮች ይኖራቸዋል፡፡ እነርሱም፡-

♦በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን ወይም ማህበራቱ በራሳቸው አዘጋጅተው አቅርበው ባስፀደቁት ዲዛይን መሰረት ግንባታው በመንግስት አካል እንዲካሄድ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ግንባታው በመንግስት

እንዲገነባላቸው የወሰኑ ማሕበራት ግንባታውን ከሚያካሂደው የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አካል ጋር የግንባታ ውል ይፈፅማሉ፡፡ ማህበራቱ በግላቸው አዘጋጅተው ባቀረቡት ዲዛይን መሰረት ግንባታው በመንግስት አካል የሚካሄድ ከሆነ በዲዛይን ለውጥ ምክንያት የግንባታው ወጪ የሚጨምር ከሆነ ልዩነቱን ለማህበሩ በተከፈተው ዝግ ሂሳብ ሙሉ በሙሉ በማስገባት ግንባታውን ከሚያካሂደው የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አካል ጋር የግንባታ ውል ስምምነት ይፈራረማሉ፡፡ ግንባታውን ለማካሄድ ውል የገባው አካል በውሉ መሰረት ግንባታውን ያካሂዳል፡፡

♦ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን ወይም ማህበራቱ በራሳቸው አዘጋጅተው ባስፀደቁት ዲዛይን መሰረት ግንባታውን በፈለጉት ተቋራጭ (ኮንትራክተር) ማስገንባት ይችላሉ፡፡ ግንባታው የሚካሄደው ማህበራቱ አዘጋጅተው በፀደቀላቸው ዲዛይን መሰረት ከሆነ በዲዛይን ለውጥ የቤቱ ዋጋ ላይ ጭማሪ ካለው ሁሉም የማህበሩ አባላት ተጨማሪውን ገንዘብ በማሕበሩ ዝግ ሂሳብ በማስገባት ወደ ተግባር መግባት ይችላሉ፡፡

## 11- የቤቶች ግንባታ ቁጥጥርና ክትትል

የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ በመንግስት ሆነ በማህበራት በሚመርጡት የግን ተቋራጭ (ኮንትራክተር) የሚካሄድ ቢሆንም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የቤቶች የዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርጉበትን የተጠናከረ አሰራር ይዘረጋሉ፡፡ በዚሁ መሰረት፤-

- የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርግ ስልጣን የተሰጠው አካል ለቤቱ የሚቀርቡ ዲዛይኖችን ያፀድቃል፡፡
- የቤቶች የግንባታ ሂደትና የሚገነቡ ቤቶች በፀደቀው ዲዛይን መሰረት መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
- የቤቶች ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ አስመልክቶ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ይልካል፡፡
- የተገነቡ መኖሪያ ቤቶች በዲዛይኑ መሰረት የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው መገንባታቸውን በማረጋገጥ ግንባታቸው የተጠናቀቁ ቤቶች በመመሪያውና በመተዳደሪየያ ደንቡ መሰረት እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

## 12- የመኖሪያ ቤቶች ርክክብ

- በማህበር የተደራጁ አባላት መኖሪያ ቤት ርክክብን በተመለከተ ማህበሩ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል ጋር በገቡት ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ አባል ቤት ርክክብ የሚፈፀመው ግን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡
- በግል ተመዝግበው በሶስተኛ አካል በመኖሪያ ቤት ስራ ማህበራት እንዲደራጁ የተደረጉ አባላት በተመዘገቡበት የቤት_ዓይነት መሰረት በየቤቱ ዓይነት በዕጣ ይከፋፈላሉ፡፡

## 13- የመመዝገቢያ ቅፆች

| ተራ ቁጥር | የቅፅ ቁጥር | የቅፅ ዓይነት |
|---|---|---|
| 1 | ቅፅ 005 | የአባልነት መመዝገቢያ ቅፅ |
| 2 | ቅፅ 006 | የማህበሩ መመስረቻ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ |
| 3 | ቅፅ 006-1 | የማህበሩ መመስረቻ ስብሰባ አጀንዳዎች |
| 4 | ቅፅ 007 | የመስራች አባላት ዝርዝር መረጃ |
| 5 | ቅፅ 007-1 | የማህበሩ አባላት ተወካይ ዝርዝር መግለጫ ሰንጠረዥ |
| 6 | ቅፅ 008 | ማህበሩ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትለት ማመልከቻ የማቅረቢያ ቅፅ |
| 7 | ቅፅ 009 | አደራጁ ለማህበሩ ለባንክ የዝግ የቁጠባ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት የመጠየቂያ ቅፅ |
| 8 | ቅፅ 010 | የህብረት ስራ ማህበሩ ለአደራጁ የምዝገባ ሰርተፊኬት የሚጠይቅበት ቅፅ |
| 9 | ቅፅ 011 | ማህበሩ አደራጁን ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ደብዳቤ እንዲፅፍለት የሚጠይቅበት ማመልከቻ |
| 10 | ቅፅ 12 | አደራጁ ለከተማው ወይም ለዞን መሬት ልማትና ማኔጅመንት የህብረት ስራ ማህበሩ የአደረጃጀት ሂደቱን የጨረሰ መሆኑን የሚገልፅበት ቅፅ |
| 11 | ቅፅ 12-1 | የማህበሩና የአባላቱ ዝርዝር መረጃ ቅፅ |
| 12 | ቅፅ 13 | አደራጁ ለማህበሩ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅበት ቅፅ |
| 13 | ቅፅ 13.1 | የመስራች አባላት ዝርዝር መረጃ |

## 15- መተዳደሪያ ደንብ-

የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር ሲደራጅ በአባላቱ ሙሉ ተሳትፎ ውይይት በማድረግ አባላቱ የሚተዳደሩበት ደንብ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በማህበሩ አባላት በውይይት ተዘርዝሮ የሚቀርብ መተዳደሪያ ደንብ ይዘት/ ርእስ እንደሚከተለው በምሳሌነት ቀርቧል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| | አንቀፅ | የመተዳደሪያ ደንቡ ርእስ |
| | አንቀፅ 1 | ስለ ህብረት ስራ ማህበሩ መቋቋም |
| | አንቀፅ 2 | የህብረት ስራ ማህበሩ ስያሜ |
| | አንቀፅ 3 | የህብረት ስራ ማህበሩ አድራሻ |
| | አንቀፅ 4 | የህብረት ስራ ማህበሩ ኣላማና ተግባር |
| | አንቀፅ 5 | የህበረት ስራ ማህበሩ መርሆዎችና እሴቶች |
| | አንቀፅ 6 | የአባልነት መስፈርት |
| | አንቀፅ 7 | በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች |
| | አንቀፅ 8 | በመኖሪያ ቤት ስራ ማህበራት የተደራጁ ቤት ፈላጊዎች |
| | አንቀፅ 9 | ስለ ስብሰባና ድምፅ አሰጣጥ |
| | አንቀፅ 10 | ስለ ምርጫ ስነስርዓት |
| | አንቀፅ 11 | ለስራ አመራር ኮሚቴ አባልነት ስለሚያበቁ መስፈርቶች |
| | አንቀፅ 12 | የስራ አመራር አካላት |
| | አንቀፅ 13 | የጠቅላላ ጉባኤ አቋም፣ ስልጣንና ተግባር |
| | አንቀፅ 14 | የስራ አመራር ምክር ቤት(ሸንጎ) ስልጣንና ተግባር |
| | አንቀፅ 15 | የስራ አመራር ኮሚቴ አቋም፣ ስልጣንና ተግባር |
| | አንቀፅ 16 | የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስልጣንና ተግባር |
| | አንቀፅ 17 | የቁጥጥር ኮሚቴ አቋም፣ ስልጣንና ተግባር |
| | አንቀፅ 18 | ስለ ክርክር አወሳሰን |
| | አንቀፅ 19 | የፅ/ቤት አደረጃጀት |
| | አንቀፅ 20 | የሃላፊነት ደረጃ |

| | | |
|---|---|---|
| | አንቀፅ 21 | የአባላት መብትና ግዴታ |
| | አንቀፅ 22 | ከአባልነት ስለመሰናበት |
| | አንቀፅ 23 | የአገልግሎት ክፍያ (መዋጮ) |
| | አንቀፅ 24 | የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ልዩ ልዩ መዛግብት |
| | አንቀፅ 25 | ደመወዝ አበልና የትርፍ ሰዓት ክፍያ |
| | አንቀፅ 26 | ወራሽነት ስለመሰየም |
| | አንቀፅ 27 | የህንፃው አጠቃቀምና አሰተዳደር |
| | አንቀፅ 28 | ማህበሩ ስሚፈርስበት ሁኔታ |
| | አንቀፅ 29 | ስለ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም |
| | አንቀፅ 30 | ሰለ መተዳደሪያ ደንብ መሻሻል |

## 15-የሚገነቡ የቤቶች ዓይነት፣ ስፋትና የቤቶች ዋጋ

| | ከተማ/ክልል | የግንባታ ዓይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት የቦታ ስፋት | ጠቅላላ የግንባታ ግምት | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ደቡብ ሃዋሳ | በG+4 አፓርትመንት | ባለ 2 መኝታ | 80 ካ/ሜ | 770,720.98 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 85 ካ/ሜ | 824,911.15 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 110 ካ/ሜ | 876,049.35 | |
| | አርባ ምንጭ፣ ወላይታ፣ ሶዶ፣ ሆሳእና | አፓርትመንት በG+3 | ባለ 2 መኝታ | 85 ካ/ሜ | 840208.61 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 926571.12 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 115 ካ/ሜ | 959128.58 | |
| | ወልቂጤ፣ቡታጅራ፣ሚዛን አማን፣ ቴፒ | በታውን ሃውስ (G+2 | ባ 2 መኝታ | 90 ካ/ሜ | 840076.79 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 105 ካ/ሜ | 912422.86 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 120 ካ/ሜ | 956890.70 | |
| | ወራቤ፣ ሀላበ፣ ይርጋ ጨፌ፣ አለታ ወንዶ፣ በቦዲቲ፣ አረካ፣ ዱራሜ፣ ቦንጋ፣ ሳውላ፣ ጂንካና ተርጫ | በታውን ሃውስ (G+ | ባለ 2 መኝታ | 80 ካ/ሜ | 204544.70 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 90 ካ/ሜ | 242378.78 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 278736.00 | |
| 2 | ትግራይ | ከG+2 በላይ አፓርትመንት | ባለ 2 መኝታ | እስከ 74 ካ/ሜ | 424,390 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | እስከ 100 ካ/ሜ | 573,500 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | እስከ 136 ካ/ሜ | 779,962 | |
| 3 | ድሬዳዋ | በታውን ሃውስ G+1 እና G+2 | ባለ 2 መኝታ | 128 ካ/ሜ | 582,400 | ዋጋው ለምዝገባ ወቅት ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡ ለማጠናቀቂያ የሚያስፈልግ ዋጋ አያካትትም፡፡ |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 160 ካ/ሜ | 728,000 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 200 ካ/ሜ | 910,000 | |
| 4 | ጋምቤላ በክልሉ ከተማ | በአፓርትመንት (G+4 እና በላይ) | ባለ 2 መኝታ | 74 ካ/ሜ | 424,390 | በዞን ዋና ከተሞች ታውን ሃውስ (G+2) ባለ 3 እና ባለ 4 መኝታ ክፍል የሚሆን ቦታ የተዘጋጀ ሲሆን ዋጋውና ስፋቱ ለክልሉ ከተማ የተቀመጠው በተመሳሳይ ይሆናል፡፡ |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 114 ካ/ሜ | 693,120 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 150 ካ/ሜ | 912,000 | |
| | በዞን ዋና ዋና ከተሞች | በታውን ሃውስ (G+2 | ባለ 3 መኝታ | 114 ካ/ሜ | 693,120 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 150 ካ/ሜ | 912,000 | |
| 5 | ቤንሻንጉል | በአፓርትመንት (G+2 እና በላይ) | ባለ 2 መኝታ | 74 ካ/ሜ | 424,390 | ከ 4 በላይ የሆኑ ማህበራት (48 እና ከዚያ በላይ አባላት) በዩኒየን ተደራጅተው High rise ህንፃ በመሃል ከተማ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲገነቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 573,500 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 136 ካ/ሜ | 779,962 | |
| | | በቪላ G+1 እና በላይ | ባለ 3 መኝታ | 114 ካ/ሜ | 693,120 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 150 ካ/ሜ | 912,000 | |
| 6 | ሀረሪ | በአፓርትመንት (G+4 እና በላይ) | ባለ 2 መኝታ | 74 ካ/ሜ | 424,390 | ከ 2 በላይ የሆኑ ማህበራት (24 እና ከዚያ በላይ አባላት) በዩኒየን ተደራጅተው High rise ህንፃ በመሃል ከተማ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲገነቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 573,500 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 136 ካ/ሜ | 779,960 | |
| | | በታውን ሃውስ (G+2) | ባለ 3 መኝታ | 114 ካ/ሜ | 693,120 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 150 ካ/ሜ | 912,000 | |
| 7 | ሶማሌ | በአፓርትመንት (G+4 እና በላይ) | በለ 2 መኝታ | 74 ካ/ሜ | 424,390 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 573,500 | |
| | | | ባለ 4 መንታ | 136 ካ/ሜ | 779,960 | |
| | | በታውን ሃውስ (G+2) | ባለ 3 መኝታ | 114 ካ/ሜ | 693,120 | |
| | | | ባለ 4 መኝተ | 150 ካ/ሜ | 912,000 | |

| | ከተማ/ክልል | የግንባታ ዓይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት የቦታ ስፋት | ጠቅላላ የግንባታ ግምት | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | አማራ | G 4 እና በላይ | ባለ 2 መንታ | 74 ካ/ሜ | 424,390 | |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 573,500 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 136 ካ/ሜ | 779,960 | |
| | | ታውን ሃውስ | ባለ 3 መኝታ | 114 ካ/ሜ | 693,120 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 150 ካ/ሜ | 912,000 | |
| 9 | ኦሮሚያ | አፓርትማ | ባለ 2 መኝታ | 80 ካ/ሜ | 400,000 | ዋጋው ለምዝገባ ወቅት ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡ ለማጠናቀቂያ የሚያስፈልግ ዋጋ አያካትትም፡፡ |
| | | | ባለ 3 መኝታ | 100 ካ/ሜ | 550,000 | |
| | | | ባለ 4 መኝታ | 110 ካ/ሜ | 700,000 | |
| | | ታውን ሃውስ | ባለ 3 መኝታ | 80 ካ/ሜ | 800,000 | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |